#ከንባብ_ጥላ_ስር !

•

የንባብ ልምዳችሁ ምን ይመስላል? ስለንባብ ጥቅም በመዘርዘር አላደክማችሁም። በእጭሩ ንባብ ሀሴት ነው። ሁሉንም ነገር ይነካል። አዕምራዊ ዕድገት ላይ ጉልህ ድርሻ አለው። በአካላዊ ዕድገት የሰው ልጅ የተመገበውን ምግብ ይመስላል። በተመሳሳይም በአዕምሯዊ ዕድገቱም የሰው ልጅ ያነበበውን ይመስላል።

አንዳንዶች ንባብ ማለት ያነበቡትን መጻሕፍ ማስታወስ ይመስላቸዋል። ሁሉንም ነገር በቃል ይዘው ማነብነብ ካልቻሉ ምንም እንዳላነበቡ ራሳቸውን ይቆጥራሉ። የተወሰኑትም በዚህ ምክንያት ንባብን እርግፍ አድርገው የተውትም አይጠፉም። ግን ንባብ ከዚህ በላይ ይሻገራል። የግድ ሁሉንም ነገር ማስታወስ አይጠበቅባችሁም። ከፊልጋችሁም ርዕሱን፣ ደራሲውን ወይም ዋና ገፀ ባህሪውን ከአዕምሯችሁ ጓዳ ድራሹ ይጥፋ። ዋናው ቁም ነገር የመጻሕፉ ቁም ነገር ምንድ ነው? ከዚህ በፊት የማታውቁት ግን መጻሕፉን በማንበባችሁ የጨመራችሁት ምንድ ነው? ...አላበቃንም እንመለስበታለን!

የምታነቡበት ሁኔታ ሁሉንም ነገር የመወሰን አቅም አለው። ለማስታወስ ነው?፣ ለህፀፅ ፍለጋ ነው?፣ ወይስ ለመደበሪያ? ለመዝናናት ወይስ አዲስ ነገር ለማወቅ?

ሁላችንም ያለፍንባቸው የ 1 ኛ፣ የ 2 ኛ ወይም የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ፖሊሲ የንባብ ህይወታችንን የተበላሸ እንዲሆን ጉልህ አስተዋፆ አበርክቷል።

ለምሳሌ በት/ቤት የምናነበው ለፈተና ወይም ህፀፅ ወይም ጥያቄ ፍለጋ ነበረ። የፈተና ንብባ ተቀዳሚ አላማው ፈተና መመለስ ነው። ያነበብነውን ቃል በቃል ወይም ተቀራራቢ ዝርዝር መልስ እንሰጣለን። ግን ችግሩ ካነበብነው ውጪ ዝርዝር ጉዳዮችን አናውቅም ወይም ለማወቅም ጥረት አናደርግም።

ህፀፅ ፈለጋ ወይም ለትችት የምናነብ ከሆነ ደግሞ ትንሽ በያዝናት ዕውቀት ውቅያኖሱን ለመንቀፍ እንሞክራለን። የሂስ ችግሩ አዲስ ዕውቀት ለመቀበል ዝግጁ አያደርገንም። ውቅያኖሱን ወደ ራሳችን ኩሬ ለማምጣት እንሞክራለን። ከነጭና ጥቁሩ ባሻገር ስላለው ምናብ ትኩረት አያደርጉም።

በትክክልና በስህተት ራሳችንን አጥረን የምናነብ ከሆነ በቀጥታ የምንቃርመውን ነገር እየገደብነው እንደሆነ መረዳት ይኖርብናል። የተለያየ አቅጣጫ እሳቤዎችን በሁለት አቅጣጫ እሳቤዎች (ትክክል ወይም ስህተት) ሳጥን ውስጥ እናስገባዋለን።

ለአንባቢዎች አንድ ግልፅ መሆን ያለበት ነገር 100 % የምታስታውሱት ወይም ያላንዳች ተቃርኖ የተስማማችሁበት መጻሕፍ ብታነቡ በእርግጠኝነት በቅርቡ ከአዕምሯችሁ እየጠፉ ይሄዳል። ስለዚህ በሁለቱም መንገድ ዕይታችን የተንሸዋረር እንዲሆን የበኩሉን አስተዋፆ አበርክቷል።

ማንበብ ግን ዝርዝር ጉዳዮችን ማስታወስ ወይም ለማሄስ አይደለም። ማንበብ ብዙ የአስተሳሰብ ዕይታዎችን መፍጠር ነው። የጠራም ምናብ መሳል ነው። የአስተሳሰብ ዕይታ፣ ምናብ እንዴት እንፈጥራለን?

ይሄንን ከመመለሳችን በፊት በቅድሚ አንድ ጥያቄ ላንሳ። ለምን እናነባለን?

ምናነበው በቅድሚያ ለመረዳት ነው። ለምሳሌ የክቡር ዶ/ር ሀዲስ ዓለማየሁን ፍቅር እስከ መቃብር ወይም የይስማዕከ ወርቁን ደርቶጋዳ እያነበባችሁ ነው እንበል። በሁለቱም አውድ ውስጥ ሆናችሁ መጻሕፍቱ ሚነግሯችሁን/ሚያስተላልፉትን ትቃርማላችሁ። በዚህ ጊዜ የሚጠቅመውን ከማይጠቅመው ትለያላችሁ። ግን አንዱን ትክክል ሌላውን ስህተት በሚል ነጥብ የምትለዩ ከሆነ በጥቂት ቀለም ሁሉንም ክፍል ለመቀባት ብቻ እየሞከራችሁ ብቻ ሳይሆን የግንዛቤ ግዛታችሁን እያጠበባችሁት መሆኑን መረዳት ይኖርባችኋል።

ማን ነበር ስህተት ተብሎ በተፈረጀ ፅሁፍ ውስጥ የሚያስተምረው ትምህርት አቅም የለውም ያለው? እናም አሁን ትክክል ስህተት እያላችሁ የምታዳሉት ነገር አድሎ መሆኑን የአስተሳሰብ ዕይታችሁ የዳበረ ሲሆን ትገነዘቡታላችሁ። ከጊዜ በኋላ ያንኑ መጻሕፍ

ደግማችሁ ስታነቡት ባለመብሰላችሁ የዘለላችሁትን አዲስ ዕውቃት ታገኛላችሁ።

አብዛኛው መጻሕፍት ከአንድ በላይ ጭብጥ ነው ያላቸው። ብዙ ቁም ነገሮች የተለያየ ቦታ መኖሩን ትገነዘባላችሁ። በማህይምነታችሁ አውቀዋለው ብላችሁ፣ ስሜት ያልሰጣችሁን፣ ካለብለስት የፈረጃችሁት ወይም በትክክል ወይም በስህተት የለያችሁት ውስጥ ዕልፍ ረብ ሀሳቦችን እንዳለፋችሁ ታስተውላላችሁ። እናም የንባብ ግብ ካለአድሎ ዕውቀት መውሰድ ነው። አዕመሯችሁን ይሄን ከተማረ ሳይታዘዝ ሚጠቅመውን ከማጠቅመው መለየት ይጀምራል። የራምፓን ወይም የኦሾን ስራዎች የሰይጣን፣ የሼክስፒርን ወይም የሁጎን ስራዎች የመላዕክት በማለት አዕሯችሁ ውስጥ አድሎ ከፈጠራችሁ ለአዲስ ዕውቀት ዝግጁ አይደላችሁም።

ሌላም ደግሞ ከትምህርት መጻሕፍት ውጪ ያሉትን ለመደበሪያነት፣ ለመዝናኛነት እንዲሆኑ ፈርጀናቸዋል።
ለመዝናኛነት ሲነበብ የመጻሕፉን አዝናኝነት እንጂ ጭብጡን ለመረዳት ከባድ ነው። እና ደግሞ ብዙ ጊዜ በመልዕክታቸው የበለፀጉ መጻሕፍ አዝናኝ ስለማይሆኑ ተመራጭ አይሆኑም። ተደባሪዎች ደግሞ ስራ ስላጡ መጻሕፍት ያነሳሉ። የነሱ አላማ የሚቃረመው ዕውቀት ሳይሆን ተራራ ሆኖ አልገፋ ያላቸውን ሰዓት ወዲያ ዞር ለማድረግ ነው። ስለዚህ አሁንም ቢሆን ስህተት ውስጥ ነን።

ከላይ ለመነካካት የሞከርናቸው የንባብ ሆኔታዎች ከእውቀት ጋር ቁማር ተጫውተን የተበላንባቸው ናቸው።

#ቸር_ጊዜ!
•
#በአንተነህ
#ሰኞ ግንቦት ፲፱፣ ፳፻፲፭